**የታቀደው የምድብ እርምጃ መቋቋሚያ ማስታወቂያ**

**አሁን ከ18 ዓመት በታች ላሉ ለዋሽንግተን የማደጎ ልጆች በሙሉ**
**ከዚህ በታች ያለውን መግለጫ የሚያሟሉ፦**

1. የ **5 ወይም ከዚያ በላይ የማደጎ ምደባዎችን** ካለዎት (እንዲሁም ባለፈው አመት ቢያንስ አንድ ጊዜ የማደጎ ቤቶችን ቀይረዋል፣ ዝርዝሮችን ከታች ይመልከቱ)።
2. ከስቴት ዉጪ ላሚገኝዘዉ አንክብካቤ ምደባ ከተላኩ **እዚያ ዉስጥ** ከነበ፤
3. ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ **የሆቴል ወይም የቢሮ ቆይታ** ከአጋጠሞዎት፤ ወይም
4. **የልጆች የረዥም-ጊዜ ታካሚ መርሃግብር (Children's Long-Term Inpatient Program "CLIP")** አልጋ እየጠበቁ ነው።

**እርስዎ ከላይ ከተገለጹት ውስጥ ከሆኑ ወይም ከላይ የተገለጹትን ውስጥ አንድ ወይም ብዙ ልጆችን የሚንከባከቡ ከሆነ፣**
**እባክዎ ይህን ማስታወቂያ በጥንቃቄ ያንብቡ.**

Para acceder a una versión de este aviso traducida en ***español***, visite https://www.dcyf.wa.gov/ds-settlement-agreement;
Để xem bản dịch thông báo này bằng ***tiếng Việt***, vui lòng truy cập https://www.dcyf.wa.gov/ds-settlement-agreement;
សម្រាប់ការបកប្រែនូវសេចក្ដីជូនដំណឹងនេះជា ***ភាសាខ្មែរ***, សូមចូលមើល https://www.dcyf.wa.gov/ds-settlement-agreement; ສໍາລັບການແປແຈ້ງການນີ້ເປັນ***ພາສາລາວ***, ກະລຸນາເຂົ້າເບິ່ງ https://www.dcyf.wa.gov/ds-settlement-agreement;
如需本通知的***中文版***，请访问https://www.dcyf.wa.gov/ds-settlement-agreement;
Перевод этого уведомления на ***русский язык***опубликован по адресу https://www.dcyf.wa.gov/ds-settlement-agreement;
***한국어***로 번역된 공지문은 https://www.dcyf.wa.gov/ds-settlement-agreement 를 방문하여 확인하실 수 있습니다;
Para sa pagsasalin ng notice na ito sa ***Tagalog***, bumisita sa https://www.dcyf.wa.gov/ds-settlement-agreement;
በ ***አማርኛ***ዚህን ማሳወቂያ ትርጉም ለማግኘት፣ እባክዎ https://www.dcyf.wa.gov/ds-settlement-agreementን ይጎብኙ;
Si aad ogeysiiskan ugu hesho ***Af-Soomaali***, fadlan booqo https://www.dcyf.wa.gov/ds-settlement-agreement.

እርስዎ *D.S. et al., v. Washington State Department of Children, Youth, and Families, et al.* የጉዳይ ቁጥር 2፡21-ሲቪ-00113 በሚባል ክስ "የምድብ አባል" ነዎት። ይህ ክስ እንደሚከተለው ቀርበዋል፦ (1) የህጻናት፣ ወጣቶች እና ቤተሰቦች መምሪያ የማደጎ ልጆች የሚያስፈልጋቸውን አገልግሎቶች እና ድጋፎች እየሰጣቸው አይደለም፤ (2) በርካታ የማደጎ ልጆች ብዙ ጊዜ መንቀሳቀስ ወይም በሆቴሎች ወይም ከስቴት ውጭ ምደባዎች ወይም CLIP መገልገያዎች ውስጥ መቆየት ነበረባቸው።

ይህ ክስ ያለፍርድ እንዲቋቋጭ የቀረበ የውሳኔ ሃሳብ አለ። እርስዎ "የምድብ አባል" ስለሆኑ መብቶችዎ ሊነኩ ይችላሉ።

በ ___ሴፕቴምበር 7_____፣ 2022፣ በዋሽንግተን ምዕራባዊ ዲስትሪክት የዩናይትድ ስቴትስ ዲስትሪክት ፍርድ ቤት ዳኛ Barbara Rothstein ፊት የፍርድ ቤት ችሎት ይኖራል። ዳኛ Rothstein የውሳኔ ሃሳቡ ማጽደቁን ይወስናሉ። ዳኛ Rothstein ማፅደቅ የምትችለው የታቀደውን የውሳኔ ሃሳብ ፍትሃዊ፣ ምክንያታዊ እና በቂ ሆኖ ካገኘችው ብቻ ነው።

**በፍርድ ቤት ችሎት ላይ ተገኝተው ማንኛውንም አወንታዊ ወይም አሉታዊ አስተያየቶችን ለዳኛው መንገር ይችላሉ።**

የውሳኔ ሃሳቡ ስምምነት መጽደቅ አለበት ብለው ካላመኑ፣ "መቃወም" እና ምክንያቱን ለዳኛዋ መንገር ይችላሉ። በጽሁፍ አስተያየቶችን በመናገር ወይም በመላክ የሚያስቡትን ለዳኛዉ መንገር ይችላሉ። ይሁን እንጂ የግድ መገኘት ወይም ማንኛውም አስተያየት መስጠት አይጠበቅብዎትም።

**የችሎት ጊዜ፦** ሴፕቴምበር 7፣ 2022፣ 1**:00 PM**
**ቦታ፦ Courtroom 16A, Seattle Courthouse for the Western District of Washington, 700 Stewart St., Seattle, WA 98101**

***ከዚህ በታች ያሉትን መመሪያዎች በመከተል ተጨማሪ መረጃ ማግኘትና ጥያቄዎችን መጠየቅ ይችላሉ። እባክዎ ስለታቀደው የውሳኔ ሃሳብ ዳኛዋን Rothstein ወይም የፍርድ ቤቱን ፀሐፊ አይደውሉ ወይም አያነጋግሩ።***

**<u>በዚህ ክስ ውስጥ ማን ተሳተፈ?</u>**

በምድብ ክስ ተመሳሳይ የይገባኛል ጥያቄ ያላቸውን አንድ ወይም ብዙ ሰዎች ቡድን ("ምድብ" የሚባለዉ) ወክለው ይከሳሉ።

ይህ ጉዳይ በWashington State Department of Children, Youth, and Families በጥገኝነት ሂደት (በዋሽን. Rev. Code § 13.34 ስር) ምደባ ውስጥ ያሉ ወይም ወደፊት ለሚኖሩ ከ18 አመት በታች ለሆኑ ልጆች ሁሉ ምድብ በመወከል እና ከሚከተሉት አንዱን ለሚያሟሉ የቀረበ ነው፡-

1. የ 5 ወይም ከዚያ በላይ የማደን ምደባዎችን አሳልፈዋል (<u>እና</u> (ሀ) ባለፈው አመት ቢያንስ አንድ ጊዜ የማደን ቤቶችን ቀይረዋል፣ አሊያም (ለ) ላለፈው አመት ወይም ከዚያ በላይ በብቁ የመኖሪያ ቤት ህክምና ፕሮግራም (QRTP) ውስጥ ገብተዋል)፤
2. ከስቴት ውጪ የቡድን እንክብካቤ ምደባዎች ተልከዋል ወይም ውስጥ ይገኛሉ፤
3. ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ የሆቴል ወይም የቢሮ ቆይታ አጋጥሞዎታል፤ ወይም
4. የልጆች የረዥም-ጊዜ ታካሚ መርሃግብር (Children's Long-Term Inpatient Program "CLIP") አልጋ እየጠበቁ ነው።

እንዲሁም የአካል ጉዳተኞች መብቶች ዋሽንግተን (Disability Rights Washington, DRW) እንደ ድርጅት ከሰሰዋል። ምድቡ እና የአካል ጉዳተኞች መብቶች ዋሽንግተን በጋራ "ከሳሾች" ይባላሉ። ክሱ በWashington State Department of Children, Youth, and Families እና ጸሃፊው ላይ ነዉ የቀረበዉ። እነዚህም አንድላይ፣ "ተከሳሾች" ወይም "DCYF" ይባላሉ።

**<u>ይህ ክስ ስለ ምንድን ነው?</u>**

ይህ ክስ DCYF ለምድቡ የሚያስፈልጋቸውን አገልግሎቶች እና ድጋፎች እየሰጠ ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ ነው።

ከሳሾች ተገቢው የማደን አገልግሎት እና ድጋፍ ከሌለ ብዙ ማደን ልጆች ከቅርብ እና ከቅርብ ቤተሰቦቻቸው ተለይተው ከተገቢው በላይ ረዘም ላለ ጊዜ እንደሚቆዩ ተናግረዋል። የማደን ልጆች ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው ሲቆዩ፣ በሚከተሉት ውስጥ መኖር ሊኖርባቸው ይችላል፦

- ከስቴት ውጭ ተቋማት፣
- የማያቋርጥ የአንድ ሌሊት የማደን እንክብካቤ ቆይታ፣ እና/ወይም
- የሆቴል ቆይታዎች/የመንግስት ቢሮዎች።

ከሳሾች እነዚህ ድርጊቶች በምድቡ ውስጥ ያሉ ህፃናት ህጋዊ መብቶችን እንደሚጥሱ ተናግረዋል። ተከሳሾቹ በምድቡ ውስጥ ያሉ ህፃናት መብት እየጣሱ መሆናቸውን ይክዳሉ። ክሱ ፍርድ ቤቱ DCYFን ማሻሻያዎችን እንዲያደርግ እንዲያስገድድ ጠይቋል። የትኛውም የምድብ አባላት እንደ "ጉዳቶች" ገንዘብ አይከፈላቸውም።

**<u>የውሳኔ ሃሳቡ ምን ይሰራል?</u>**

ከሳሾቹ እና ተከሳሾቹ ለችሎት ከመቅረብ ይልቅ " የዉሳኔ ሀሳብ ስምምነት" ላይ ተደራድሯል። ተዋዋይ ወገኖቹ ለምድብ የዉሳኔ ሀሳብ ስምምነትን እንዲያፀድቁ ዳኛ Rothsteinን ጠይቀዋል።

***ይህ ማስታወቂያ የዉሳኔ ሀሳብ ስምምነት ማጠቃለያ ነው፡-***

*የዉሳኔ ሀሳቡ ስምምነት አገልግሎቶቹን ለማሻሻል ለ DCYF የተዘጋጀ እቅድ ነዉ። እነዚህም ማሻሻያዎች የሚከተሉትን የሚያካትቱ የአሰቃቂ ሁኔታ መረጃ ያለው፣ በባህል ምላሽ የሚሰጥ፣ እና LGBTIQA+ ከስቴት ውጭ፣ ሆቴል/ቢሮ እና የአንድ ሌሊት የማደጎ ምደባ አማራጮችን የሚያረጋግጡ ናቸው፡-*

***ታዳጊ የጎልማሶች መኖሪያ ቤት ፕሮግራም* (Emerging Adulthood Housing Program)**፡- DCYF *ከአስራ ስድስት እስከ ሃያ አመት የሆናቸው ወጣቶች በማደጎ ወይም በተራዘመ የማደጎ ልጅ ለፕሮግራሙ ብቁ ለሆኑ እና ከቤተሰብ ጋር ከመኖር ይልቅ እራሳቸውን ችለው መኖርን የሚመርጡ በርካታ የሚደገፉ የቤት መርሃግብሮችን አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደርጋል።*

***ፕሮፌሽናል ቴራፒዩቲክ የማደጎ ልጅ ወላጅነት***፡- DCYF *የእድገት ችግር ወይም የባህርይ ጤና ፍላጎቶችን ያለባቸውን ልጆችን ለመንከባከብ ለህክምና አሳዳጊ ወላጆች ባለሙያዎች የውል እና የፈቃድ ምድብ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደርጋል።*

***የስቴት-አቀፍ ሃብ የቤት ሞዴል ፕሮግራም***፡- DCYF *የማደጎ ልጆችን የሚደግፉ፣ የተራዘሙና የተመረጡ ቤተሰቦች ስቴት-አቀፍ የ* Hub Home Model (HHM) *ፕሮግራም በማዉጣት ይተገበራል።*

*እንዲሁም፣* DCYF *ምደባዎች በሚከተሉት ተግባራት የበለጠ ስኬታማ እንዲሆኑ ለማገዝ የተግባር ማሻሻያዎችን ያደርጋል፡-*

***የፈቃድ መስጫ ደረጃዎችን መከለስ***፡- DCYF *ለታዳጊ እንክብካቤ ምደባዎች የፈቃድ መስፈርቶቹን የበለጠ ለእድገት ተስማሚ ለማድረግ እና ተለዋዋጭ የወጣቶችን ፍላጎቶች ለማሟላት ያስተካክላል።*

***የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ፡-*** DCYF *እነዚህን የማሻሻያ ጥረቶች አስመልክቶ ባለድርሻ አካላትን ግብአትን ለመጠየቅ፣ ለመሰብሰብ እና ሪፖርት ለማድረግ ብቁ ባለድርሻ አካላትን ይቀጥራል፡-*

***የዝምድና ተሳትፎ ክፍል***፡- DCYF *ስቴት-አቀፍ የዝምድና ተሳትፎ ክፍል* (KEU) *የሚያቋቁም ሲሆን ይህም የምድብ አባላት የተራዘመ ቤተሰብ አባላትን እና ጓደኞችን ለመለየት እና ለማሳተፍ ቤተሰብን በደህና እንዲገናኙ ወይም አብረው እንዲቆዩ ያደርጋል።*

***ሪፈራሎች እና ሽግግሮች***፡- DCYF *ልጆች እና ወጣቶች በሕይወታቸው ውስጥ ለውጦች ሲከሰቱ በተሻለ ሁኔታ የሚረዷቸውን የሪፈራል እና የሽግግር መመሪያዎችን ያዘጋጃል።*

***የቤተሰብ ቡድን እቅድ ማውጣት፡-*** DCYF *የልጁን እና የቤተሰብ ምርጫዎችን እና ውሳኔዎችን በተሻለ መልኩ ለመደገፍ የእነርሱን የጋራ እቅድ ስብሰባ* (SPM) *እና የቤተሰብ ቡድን ውሳኔ ስብሰባ* (FTDM) *መመሪያዎችን እና ልምዶችን ያሻሽላል።*

***የቡድን እንክብካቤ ምደባ***፡- DCYF *ልጅን በቡድን እንክብካቤ መስጫ ተቋም ውስጥ ማስገባት ተገቢና አስፈላጊ መሆኑን ለመወሰን የበለጠ አጠቃላይ የግምገማ ሂደት ያቋቁማል።*

***የትግበራ ዕቅድ***፡- DCYF *የገባውን ቃሎች እንዴት እንደሚፈጽምና አዲሶቹ አገልግሎቶች መቼ እንደሚገኙ የሚገልጽ የትግበራ ዕቅድን ያዘጋጃል። ረቂቅ ዕቅዱ የመጨረሻ ከመሆኑ በፊት ለይፋ አስተያየት ይቀርባል።*

**ቁጥጥር፡-** Kathleen Noonan በዚህ ውሳኔ ሃሳብ ስምምነት እንደ የDCYFን ተገዢነት ተቆጣጣሪ ትሾማለች። ተቆጣጣሪው የDCYFን ትግበራ ዕቅድ ይገመግማል፣ የDCYFን አፈጻጸም በተመለከተ ቀጣይነት ያለው መረጃን ይገመግማል፣ እንዲሁም የDCYF ውሳኔ ሃሳብ ስምምነት ውሎችን በመተግበር ላይ ስላለው ዕድገት አመታዊ ሪፖርቶችን ያቀርባል።

**የውሳኔ ሃሳብን ማገባደድ፡-**

DCYF ሁሉንም ስምምነት ላይ የተደረሱ ለውጦች እንዳደረገ ዳኛው እስኪወስኑ ድረስ DCYF የውሳኔ ሃሳብ ስምምነቱን መተግበሩን መቀጠል አለበት። ውሳኔውን በሚሰጥበት ጊዜ፣ ዳኛው የሚከተሉትን ይሆኑ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ታሳቢ ያደርጋል፡-

አዳድስ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ሪፈር ከታደረጉ ወይም ከጤቁ ዉስጥ - 90 % የሚሆኑ ሪፈር ከተደረጉ ወይም ጥያቄ ካቀረቡ ግዜ ተነስተዉ በ 60 ቀናት ዉስጥ ይገለገላሉ፤

- ሆቴል/ቢሮ እና ከማታ እስከ ማታ የማደሪ እንክብካቤ ምደባዎች ቀርተዋል፤

- ልዩ ሁኔታዎች ስራ ላይ ካልዋሉ በስተቀር፣ ከስቴት ውጭ ባሉ መገልገያዎች ውስጥ ያሉ የምደባዎች ብዛት ወደ 10 ወይም ከዚያ በታች ቀንሷል፤ እንዲሁም

- ከአምስት በላይ ምደባ የነበራቸው ልጆች ብዛት በበቂ ሁኔታ ተቀንሷል።

ክሱ ምንም አይነት የገንዘብ ኪሳራዎችን አይጠይቅም፣ ስለሆነም **የዉሳኔ ስምምነት ለማንኛውም ክፍል አባላት ምንም አይነት የገንዘብ ኪሳራ መከፈልን አያካትትም።** ከላይ የተጨምቆ የተቀመጠዉን ለዉጦችን ብቻ ነዉ የሚጠይቀው።

የዉሰኔ ሃሳቡ ውል በተከሳስሽ መከፈል ያለበት የጠበቆች ወጪ እና ክፍያዎችን ለከሳሾች ጠበቃ ያቀርባል። ከሳሾች ምንም አይነት ክፍያ ከከሳሽ ልጆች አይጠይቁም እንዲሁም የምድብ አባላት ከዚህ ክስ ጋር በተያያዘ ገንዘብ፣ ክፍያ ወይም ማንኛውንም አይነት ክፍያ አይከፍሉም። ተዋዋይ ወገኖች አሁን የጠበቃ ክፍያዎች እና ወጪዎች አቅርቦትን በመደራደር ላይ ናቸው። የከሳሾችን የጠበቆች ክፍያዎች እና ወጪዎች በኦገስት 5፣ 2022 ወይም በኋላ በDRW ድረገፅ በ https://www.disabilityrightswa.org/cases/d-s-v-washington-state-department-of-children-youth-and-families እና National Center for Youth Law ድረገፅ በ https://youthlaw.org/settlement-ds-v-washington-state-dcyf ላይ ማግኘት ይችላሉ።

ዳኛው ለከሳሾች ወይም ለተከሳሾች ድጋፍ ለመስጠት እንዲወስን ለመጠየቅ ወደ ችሎት ከመሄድ ይልቅ፣ DCYF እና ከሳሽ ዳኛው የዉሳኔ ሃሳብ ስምምነቱን እንዲያፀድቀው ጠይቀዋል።

የዉሳኔ ሃሳብ ስምምነቱን በሙሉ የመገምገም መብት አለዎት። የመቋቋሚያ ስምምነት ቅጂ ለማግኘት፣ እባክዎ ከታች ያሉትን መመሪያዎች ይከተሉ ወይም በ DRW ድረገፅ በ https://www.disabilityrightswa.org/cases/d-s-v-washington-state-department-of-children-youth-and-families እና National Center for Youth Law ድረገፅ በ https://youthlaw.org/settlement-ds-v-washington-state-dcyfን ይጎብኙ።

**መወሰን እና አለመወሰን ዳኛዉን ለመርዳት ስለ ውሉ የሚሰማዎትን ለዳኛው የመንገር መብት አለዎት።** ይህንንም በጽሁፍ አስተያየቶችን በመላክ፣ በአካል መገኘት እና/ወይም በመጨረሻው የማጽደቅ ችሎት ላይ በመመስከር፣ ወይም በሁለቱም ማድረግ ይችላሉ። ይህንን እንዴት ማድረግ እንደሚቻል መመሪያዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል።

***<u>አማራጮቼ ምንድናቸው?</u>***

**Disability Rights Washington ለፍርድ ቤት እንዲያጋራ አስተያየትዎን ይስጡት፡-** ለDisability Rights Washington (DRW) በኢሜይል፣ በደብዳቤ ወይም በስልክ አስተያየቶችን መስጠት ይችላሉ። ፍርድ ቤቱ እንዲመለከተው አስተያየትዎ ከኦገስት 12፣ 2022 **ባልበለጠ**

**ጊዜ ውስጥ መግባት** አለበት። ለ DRW የሚሰጡ አስተያየቶች ከሚከተሉት ውስጥ ወደ ማናቸውም ሊላኩ ይችላሉ፡-

በፖስታ፡- Disability Rights Washington, 315 5th Ave. S., Suite 850, Seattle, WA 98104
በኢሜይል፡- DSSettlement@dr-wa.org
በስልክ፡- 206-324-1521 or 1-800-562-2702

ድብዳቤዎን መፈረም እንዲሁም እርስዎን እንዴት ማነጋገር እንደሚቻል (አድራሻ፣ ኢሜይል፣ ስልክ ቁጥር፣ ወዘተ.) የእርስዎን ስም እና መረጃ ማካተት አለብዎት። DRW ከችሎቱ በፊት በተቀበሉ 7 ቀናት ውስጥ እና በዳኛ ወይም ኦገስት 22፣ 2022 አስተያየቶችዎን ለዳኛዉ እና ለDCYF ጠበቆች ያጋራል።

**በፍትሃዊነት ችሎት ላይ ይገኙ፡-** የዉሳኔ ሀሳብ ስምምነቱ ፍትሃዊ፣ ምክንያታዊ እና በቂ መሆኑን ለመወሰን ችሎቱ ለህዝብ ክፍት ይኖራል። ችሎቱ በ 1:00 P.M. በሴፕቴምበር 7፣ 2022፣ በ700 Stewart Street፣ Seattle, WA 98101 Courtroom 16A በሚገኘው የፌዴራል ፍርድ ቤት ይካሄዳል።

አስተያየትዎን ለዳኛው ለማጋራት በችሎቱ ላይ ተገኝተው መናገር ይችላሉ። ከችሎቱ በኋላ ስምምነቱ መጽደቅ እንዳለበት ወይም እንደሌለበት ፍርድ ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል።

የችሎቱ ቀን፣ ሰዓቱ ወይም ቦታው ከተቀየረ ወይም ስለ ችሎቱ ሌላ መረጃ ከተቀየረ፣ አዲሱ መረጃ በ DRW ድረገፅ በ https://www.disabilityrightswa.org/cases/d-s-v-washington-state-department-of-children-youth-and-families እና National Center for Youth Law ድረገፅ በ https://youthlaw.org/settlement-ds-v-washington-state-dcyf ላይ ይለቀቃል። ስለ ለውጡ ተጨማሪ ማስታወቂያ አይላክልዎትም።

ዳኛው ለየት ያለ ውሳኔ ለመወሰን ካልወሰኑ በቀር፣ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ዳኛው በችሎቱ ላይ ወይም ከዚያ በፊት ያልቀረቡ ተቃዉሞዎችን ግምት ዉስጥ አያስገቡም።

**ተጨማሪ መረጃ እንዴት ማግኘት ወይም ጥያቄዎችን መጠየቅ እችላለሁ?**

የዉሳኔ ሀሳብ ስምምነት ቅጂ እና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎች፣ በችሎቱ ላይ እንዴት እንደሚገኙ ጨምሮ፣ በ DRW ድረገፅ በ https://www.disabilityrightswa.org/cases/d-s-v-washington-state-department-of-children-youth-and-families እና National Center for Youth Law ድረገፅ በ https://youthlaw.org/settlement-ds-v-washington-state-dcyf ላይ ይገኛል። እንዲሁም Disability Rights Washingtonን ማንኛውም ጥያቄ በመያዝ በቀጥታ ማነጋገር ወይም የዉሳኔ ሀሳብ ስምምነት ቅጂን በፖስታ በሚከተለው መጠየቅ ይችላሉ፡- Disability Rights Washington, 315 5th Ave. S., Seattle, WA 98104 ወይም በኢሜይል ወይም በስልክ በ፡- 1-800-562-2702 እና DSSettlement@dr-wa.org።

****እባክዎ ወደ ዳኛ Barbara Rothstein ወይም የፍርድ ቤቱ ፀሐፊ አይደውሉ****

*እነሱ ስለ ክሱ ወይም የዉሳኔ ሀሳብ ስምምነትን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን አይመልሱም። ሆኖም ወደ U.S. ፀሃፊ ፅህፈት ቤት በመሄድ ለፍርድ ቤት የቀረቡ ማናቸውንም ያልታሸጉ ቁሳቁሶችን መገምገም ትችላለህ። ለ Western District of Washington የድስትሪክት ፍርድ ቤት በ 700 Stewart Street, Seattle, WA 98101 የፅሀፈት ቤቱ ቢሮ (Clerk's Office counter) ቅዳሜ እና እሁድ 9:00 A.M. እስከ 4:00 P.M. ከፍርድ ቤት በዓላት በስተቀር ክፍት ነው። እንዲሁም በዚህ ኬዝ ላይ የፍርድ ቤቱን ሰነድ በክፍያ፣ በፍርድ ቤት የህዝብ ተደራሽነት በኩል በ https://pacer.uscourts.gov/ ሲስተም ላይ ለፍርድ ቤት ኤሌክትሮኒክ መዛግብት (PACER) በመክፈል ማግኘት ይችላሉ። በዚህ ጉዳይ ላይ በህዝባዊ መዝገብ ውስጥ ያሉ ዶኩሜንቶችን ለመገምገም፣ ወደ ጉዳይ ቁጥር 2: 21-cv-00113 ይሂዱ።*